**በጉምሩክ ኮሚሽን**
**የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት**
**CUSTOMS COMMISSION**
**ADDIS ABABA KALITI CUSTOMS BRANCH OFFICE**
**የሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የውስጥ ማስታወሻ**

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 101/12

ቀን: 03/07/2012 ዓ.ም

ለ፡- የንግድ ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፡- የንግድ ያልሆኑ የገቢ ዕቃዎች የስራ ሂደት
ለ፡- ኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፡- ኢንተለጀንስና ኮንትሮባንድ ክትትል የሥራ ሂደት
ለ፡- ገላን ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ
ለ፡- ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት

ከ፡- ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
ኢ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ፍቃዱ አማረ /ተወካይ/

ከጉምሩክ ኮሚሽን በቁጥር 6.1/0341/12 በቀን 02/07/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቁጥር ውምክሪአደ/0232/2020 የካቲት 20 ቀን 2012 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ በኤል ሲ (LC) ወይም በሲ.ኤ.ዲ (CAD) ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች በባንኮች በኩል ክፍያ የሚፈጸመው ሰነዱ በባንክ በኩል ሲመጣና ምንም አይነት ዕፀፅ (Discrepancy) በተለይ የዋጋ እና የዕቃ ለውጥ የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነና በሌላ በኩል በቅድሚያ ክፍያ (TT) የመሳሰሉትን ሰነዶች በቅድሚያ ክፍያ ስርዓት (TT) ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች የኮሜርሻል ኢንቮይስ፣ የጭነት ሰነድ፣ ፓኪንግ ሊስት የመሳሰሉ ሰነዶች በቀጥታ ለአስመጪው የሚላኩና አስመጪው ከባንክ የተሰጠውን የጉምሩክ ዕቃ ማውጫ ኮፒዎች አጣምሮ ለጉምሩክ በማቅረብ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸመው ቀጥታ አስመጪው በሚያቀርበው ሰነድ መሰረት በመሆኑ ባንኩ ባስቀመጠው ዋጋ ወይም በተፈቀደው ዕቃ መሰረት ወደ አገር እየገባ መሆን አለመሆኑ ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱን ጠቅሶ በቅድሚያ ክፍያ(TT) ወደ አገር ለሚገቡ ተሽከርካዎች ከላይ በተጠቀሱት (የማስጫኛ ሰነድ፣ ኮሜርሺያል ኢንቮይስ፣ ፓኪንግ ሊስት) የመሳሰሉት ሰነዶች ባንኩ ጋር ቀርበው ሲረጋገጥ እና የባንኩ ማህተም ተደርጎ ሲመጣ ብቻ ማስተናገድ እንዲቻል አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም ከላይ በተገለጸው መሠረት አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብኩ ለአፈጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ የተላከው 2 ገጽ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (አምራች ወጪና ሌሎች ጣቢያዎች)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (የንግድ ገቢ ዕቃዎች ኦፕሬሽን)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (ህግ ተገዥነት)
ለ፡- ጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
ለ፡- ደህረ-ዕቃ አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፡- ደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ የስራ ሂደት
ኢ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤ

